



በማኅበረ ቅዱሳን የአሜሪካ ማዕከል ትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ክፍል የኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓት እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት ጠብቆ እየተዘጋጀ በየሚሶ ዓመቱ የሚወጣ የኤሌክትሮኒክስ መጽሔት

፳ኛ ዓመት ቁጥር ፪ ሚያዝያ ፳፻፫ ዓ.ም.

## ማውጫ

የአሜሪካ ማዕከል መልእክት ........................................... 1
የሐመረ ኖኅ እንግዳ (ቆይታ ከብፁዕ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ ጋር) 2
ዜና ............................................................................ 4
ስብከተ ወንጌል ........................................................... 8
ኪነ ጥበባት ................................................................ 11
ለሕፃናት .................................................................... 12

# የአሜሪካ ማዕከል መልእክት

## 19 ዓመት እንደ አንድ ዓመት

እንኳን አደረሳችሁ። ከበዓለ ትንሣኤው እስከ እመቤታችን ልደት፣ ከማኅበራችን 19ኛ ዓመት ምሥረታ እስከ በዓለ ዕርገት ብሎም በዓለ ኀምሳ። ሰሙናቱ ድርብ በዓላት የበዙበት ስለሆነ በደምሳሳው "እንኳን አደረሳችሁ" ብንል ለሁሉም ያስኬዳል።

የአገልግሎት ማኅበራችን በቤተ ክርስቲያናችን በምልዓት እና በስፋት እንዲያገለግል ዕውቅና እና ይሁንታ ካገኘ የአንድ ወጣት ዕድሜ ያስቆጠረበት ወራት ላይ ደርሰናል። በ1984 ዓ.ም. የግንቦት ልደታ በዓል ላይ ቅዱስ ፓትርያርኩ እና ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት እንዲሁም ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንና ምዕመናን፣ ምዕመናት በተገኙበት አገልግሎቱን አስባርኮ የጀመረው ማኅበረ ቅዱሳን በዚህ የአገልግሎት ዘመኑ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎችን በቃለ እግዚአብሔር እየተኮተኮተ ከማውጣቱም ባሻገር በገዳማትና አድባራት ያለውን መጠነ ሰፊ ችግር ለመቅረፍ በዓይነቱ ታሪካዊ ሊባል የሚገባው የምዕመናን መነቃቃት እና እንቅስቃሴን አስተዋውቋል።

በዚህ የገዳማት እና አድባራት እርዳታ ውስጥ ከምዕመናን እርዳታዎችን በማስተባበር ትልቅ የድጋፍ ምንጭ ከሆኑት ማዕከላት መካከል ይኸው የእኛው የአሜሪካ ማዕከላችን አንዱና ወሳኙ ነው። ቅድመ እግዚአብሔር ሊያስመሰግን የሚችል፣ በታሪክም ውስጥ ሊዘነጋ የማይችል ተግባር ተከናውኗል። አሁንም እንደቀጠለ ነው። በአሁኑ ወቅት ገዳማትና አድባራትን መርዳት፣ አብነት ትምህርት ቤቶችን ማስፋፋትና የተስፋፉትንም እንዳይበተኑ መጠበቅ፣ አበው ሊቃውንት ወንበራቸውን አጥፈው ከበዓታቸው እንዳይፈናቀሉና ተማሪዎችም እንዳይበተኑ በማድረጉ ሒደት ማኅበረ ቅዱሳን የመሪነቱን ድርሻ ከመውሰዱም በላይ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ደግሞ ይህንኑ ዓላማ ያነገቡ ብዙ ወገኖች እንዲፈጠሩ ትልቁን ድርሻ አበርክቷል።

19 ዓመታት በአገልግሎት በመቆየታችን ግን ችግሮቹን በ19 ዓመት ቀንሰናቸዋል ማለት አይደለም። ይልቁንም ከቀድሞው በበለጠ ጊዜያችንን፣ ጉልበታችንን እና ገንዘባችንን የሚጠይቁ፣ በጸሎት እንድንበረታ እና እንድንቋቋማቸው የሚፈልጉ ብዙ ችግሮች አሉ። ከውስጥም ከውጪም። ከውስጥ መናፍቃን እና የእነርሱ ተላላኪዎች፣ ከውጪ ደግሞ አጽራረ ቤተ ክርስቲያን ፈተና መሆናቸውን ቀጥለዋል። ገዳማቱ እና አድባራቱ ትልቅ የዕድገት እመርታ ቢያሳዩም መጠነ ሰፊ ችግራቸው አሁንም እንዳለ ነው። የማኅበራችንን አገልግሎት እና ዓላማ ያልተረዱ፣ ድጋፍ በመስጠት ለሰማያዊው መንግሥት ሊያበቃን የሚችል ሥራ አብረን ልንሠራ የምንችላቸው አካላት እንቅፋት መሆናቸው እንደቀጠለ ነው። ይህንን ሁሉ በመቅረፉ ሂደት በተለይም እኛ አባላት ትልቅ ኃላፊነት ይጠበቅብናል። ለዚህም ነው የ19 ዓመቱን አገልግሎት እንደ አንድ ዓመት ብቻ በመቁጠር ለበለጠ ሥራ ራሳችንን ማዘጋጀት ያለብን የምንለው።

ስለዚህ በዚህ የ19ኛ ዓመታችን ክብረ በዓል ሰሙን በውጪ አገር የምንገኝ አባላትም በመላዋ ኢትዮጵያ ከገጠር እስከ ከተማ ተሰማርተው የቤተ ክርስቲያን ልጅነት ግዴታቸውን በመወጣት ላይ እንደሚገኙት ወንድም እህቶቻችን ጸንተን ልንቆም እና ለማገልገል እንድንችል ልንነቃ ይገባናል። ዘመኑ የስንፍና አይደለም። ለስንፍና እና ለሰበብ ጊዜ ሊኖረን አይገባም። የአቅማችንን በመጣር የበኩላችንን ሁሉ ልናደርግ ያስፈልገናል። በረከት የምናገኘውም፣ በልጅ ልጆቻችን የምንመሰገነውም፣ በማይቀረው ሞት ስንጠራም "እናንተ የአባቴ ቡሩካን" የሚለውን ቃለ ሕይወት የምንሰማውም በዚሁ ነው።

ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን

# የሐመረ ኖኅ እንግዳ

## “…መለያየት መጨረሻው ማንነትን አጥቶ መጥፋት ነው”

## ቆይታ ከብፁዕ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ ጋር

ገና በልጅነታቸው በውስጣቸው የተፈጠረውን የመንፈሳዊ ዕውቀት ጥማት ለማርካት ወደ ጻድቁ አቡነ ተክለ ሐዋርያት ገዳም በመግባት የተማሩ ሲሆን በገዳሙ ቆይታቸው በዲቁናና በገዳሙ ግምጃ ቤት ኃላፊነት አገልግለዋል። ከዚያም ወደ አዲስ አበባ በመሄድ በቀጨኔ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን በዲቁና፣ በምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም በቅስና አገልግለዋል። በዚሁ ገዳም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቅቀው ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ በመግባት በነገረ መለኮት የዲግሪ ባለቤት ለመሆን በቅተዋል። ከሌሎች የትምህርት ተቋማትም በተለያዩ ዲፕሎማዎች ተመርቀዋል። ዛሬም በሰሜን አሜሪካ ለማስተርስ ዲግሪያቸው በመማር ላይ ይገኛሉ።

ጵጵስና ከተሾሙ በኋላ የምዕራብ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፣ የሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ ዲን በመሆን አገልግለዋል፤ ዛሬም የሰሜን ምዕራብ አሜሪካ ካሊፎርኒያ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ። ብፁዕ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ በሰሜን አሜሪካ የምዕራብ ስቴቶችና የካሊፎርኒያ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና የቅዱስ ሲኖዶስ አባል።



ብፁዕ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ

የሕይወት ተሞክሯቸውን፣ በተመደቡበት ሀገረ ስብከት ምን እየሠሩ እንዳሉና ምን ሊሠሩ እንዳቀዱ፣ ለቤተ ክርስቲያን ያላቸውን ዕቅድና ምኞት ጠይቀን መልስ ሰጥተውናል። ብፁዕ አባታችንን ከልብ እያመሰገንን ወደ ሙሉ መልእክቱ እናሸጋግራችሁ። መልካም ንባብ።

**ሐመረ ኖኅ፡-** የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የትና እንዴት ጀመሩ?

**ብፁዕ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ፡-** በቅድሚያ የሐመረ ኖህ የክብር እንግዳ ሆኜ በመቅረቤ በእግዚአብሔር ስም አመሰግናለሁ፤ እግዚአብሔር ይስጥልኝ እላለሁ።

የእኔ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት አጀማመር በጣም የሚደንቅ የእግዚአብሔር ተአምር አለው። ይህም ማለት ቤተሰቦቼ ያልተማሩ ገበሬዎች ናቸው። ፊርማ እንኳ በጣታቸው ነው የሚፈርሙት። እኔም ራሴ ትልቅ ከሆንኩና ራሴን ካወቅኩ በኋላ ነበር የቄስ /የቆሎ/ ትምህርት ቤት የገባሁት፤ ማለትም ከብቶች ሳግድ /ስጠብቅ/ ገና ፊደል እንኳ ሳልቆጥር ሃሌ ሉያ ቅዱስ ቅዱስ እያልኩ ማዜም እወድ ስለነበር ለጥምቀት ታቦት ወጥቶ ሕዝቡ ሲያጅብ ካህናቱ በማኅሌት ሲያሸበሽቡ በማየት በዚህ መነሻነትና በፈቃደ እግዚአብሔር ወደ ቄስ ትምህርት ቤት ገባሁ።

ከዚያ በኋላ እኔ ከምኖርበት አቅራቢያ ወይም አካባቢ ወደሚገኘው የጻድቁ አቡነ ተክለ ሐዋርያት ገዳም ገባሁና ብዙ ዓመት በዚያ ቆይቼ መንፈሳዊ ሕይወትና የዲቁና አገልግሎት በአጠቃላይ መንፈሳዊ ትምህርት ከዚያ ጀመርኩ፤ በኋላም በዚሁ ገዳም ውስጥ የገዳሙ ግምጃ ቤት /ንብረት ክፍል/ ኃላፊ በመሆንና የደከሙ አበው መነኮሳትን በመርዳት እንዲሁም በልዩ ልዩ የሥራ ዘርፍ ገዳሙን አገልግያለሁ።

ይህ እንግዲህ ዲያቆን ሳለሁ እንደ ባህታዊ ሆኜ ያገለገልኩት አገልግሎት ሲሆን ብዙ በረከትና ጸጋ ያገኘሁበት ከመሆኑም በላይ የኑሮዬንም አቅጣጫ ያወቅኩበት ስለሆነ ደብረ ጽሙና ገዳም ታላቅና ጸጋ እግዚአብሔር የበዛበት ቦታ ነው ብዬ መመስከር እችላለሁ ማለት ነው። ከዚህ በኋላ ወደ ከተማ በመምጣት በአዲስ አበባ በቀጨኔ መድኃኔዓለም በዲቁና፣ በምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም በቅስና አገልግያለሁ። አገልግሎትን ከሚያጠናክሩና ከሚረዱ ነገሮች አንዱ ትምህርት መሆኑን በመረዳት በዚሁ በምስካየ ኅዙናን ገዳም ሳለሁ ዘመናዊ ትምህርት በማጠናቀቅና ወደ ዩኒቨርሲቲ በመግባት ከቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ለአምስት ዓመታት ተምሬ በነገረ መለኮት በዲግሪ ተመርቄአለሁ። ከተለያዩ ኮሌጆችም የተለያዩ ዲፕሎማዎች አግኝቻለሁ። በአሁኑም ሰዓት የማስተርስ ዲግሪዬን እየሠራሁ እገኛለሁ፤ ይህም የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ለማሳደግ ይረዳኛል ብዬ አስባለሁ።

**ሐመረ ኖኅ፡-** ወደ ሰሜን አሜሪካ ከመምጣትዎ በፊት በየትኞቹ አህጉረ ስብከት አገልግለዋል?

**ብፁዕ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ፡-** ወደ ሰሜን ምዕራብ አሜሪካ ከመምጣቴ በፊት የምዕራብ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሆኜ ሠርቻለሁ። በተጨማሪም የሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ኮሌጅ ዲን በመሆን አገልግያለሁ፤ እንዲሁም እንደ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ያሉ ዓለም አቀፍ ስብሰባዎችን ከሀገር ውጭና በሀገር ውስጥ በመካፈል ልዩ ልዩ ሽልማትና የምስጋና ደብዳቤዎችን ተቀብያለሁ።

በመጨረሻም ቅዱስ ሲኖዶስ ወደ ሰሜን አሜሪካ ተዛውሬ እንዳገለግል ስለመደበኝ በአሁኑ ሰዓት የሰሜን ምዕራብ አሜሪካ ካሊፎርኒያ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሆኜ በማገልገል ላይ እገኛለሁ።

**ሐመረ ኖኅ፡-** የሰሜን ምዕራብ አሜሪካ ካሊፎርኒያ ሀገረ ስብከት ከተመሠረተ ምን ያህል ጊዜ ሆኖታል? ምንስ እየተሠራ ይገኛል? የአጭርና የረዥም ጊዜ የትኩረት አቅጣጫውስ ምንድን ነው?

**ብፁዕ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ፡-** የሰሜን ምዕራብ አሜሪካ ካሊፎርኒያ ሀገረ ስብከት ከተመሠረተ አምስት ዓመት የሚሆነው ሲሆን በሥሩም ብዙ አብያተ ክርስቲያናት በተለያዩ ስቴቶች ይገኛሉ። ሀገረ ስብከቱ ከስያሜ ያለፈ ለሀገረ ስብከት የሚያስፈልጉ ነገሮች የሉትም። የአንድ ሀገረ ስብከት ያለመንበር መኖር ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን አይደለም። ይህ ሀገረ ስብከት ግን መንበረ ጵጵስና፣ ሊቀ ጳጳሱ የሚጸልይበት፣ ሥልጣነ ክህነት /ዲቁና፣ ቅስና፣ ቁምስና/ የሚሰጥበትና ሌሎችም የክህነት ሥራዎች የሚሠሩበት፣ ቡራኬ የሚሰጥበት፣ የሊቀ ጳጳሱ ጽ/ቤትና መኖሪያ ቤት እንዲሁም የካህናት ማሠልጠኛና የስብከተ ወንጌል አዳራሽ የሌለው በመሆኑ ለመኖሪያ እንኳ በየአፓርትመንቱ እየተንከራተትኩ እገኛለሁ።

ምን እየተሠራ ይገኛል ለሚለው ጥያቄ በአሁኑ ሰዓት የሀገረ ስብከት ሕንጻ አሰሪ /ግዥ/ ኮሚቴ ተቋቁሞ በየቦታው ንዑሳን ኮሚቴዎችን አዋቅሮ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። ለዚህም ማንኛውም ክርስቲያን ኮሚቴውን ሊያግዝና ሊረዳ ይገባዋል እላለሁ። ወደፊት ልንሠራ ያቀድናቸው የሥራና የትኩረት አቅጣጫን በተመለከተ እንደ ድረ ገጽ ያሉትን የዘመኑ ቴክኖሎጂን ተጠቅሞ ትምህርተ ወንጌልን ማስፋፋት፣ አብያተ ክርስቲያናት የበለጠ እንዲጠናከሩና ለምዕመናኑ የሚገባውን አገልግሎት እንዲሰጡ ማገዝ ዋነኛው ሲሆን ሌላው የተጠናከረና የተደራጀ የሀገረ ስብከቱ መንበረ ጵጵስና እንዲኖር ማድረግ የሚለው ነው።

***ሐመረ ኖኅ፦*** የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሀገር ቤትና በውጭ /በዳያስፖራ/ ያለውን መንፈሳዊ እንቅስቃሴ እንዴት ያነጻጽሩታል? ያሉትስ ፈተናዎች ምንድን ናቸው?

***ብፁዕ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ፦*** የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሀገር ቤት በኩል ያለውን ስንመለከት በጣም የተለየየ ሆኖ አገኝቼዋለሁ። ይህም ማለት ሀገር ቤት ያለችው ቤተ ክርስቲያን ችግር የለባትም ማለት ሳይሆን ችግሩ እንደ ውጭው የከፋ አይደለም ብዬ አስባለሁ። ሌላው ችግር እንዳለ ሆኖ ቢያንስ የቤተ ክርስቲያኒቷን የአሠራር መዋቅር ጠብቆና ተከትሎ መሄድ ስላለ ይህ ዓይነቱ አሠራር ቀጥተኛና ትክክለኛ በመሆኑ ልዩ ያደርጋታል ብዬ አምናለሁ።

ወደ ውጭው ስንመጣ በተለይም በአሜሪካ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ችግር ውስጥ ነው ያለችው። ይህም ማለት አብዛኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚለውን ስም ሰውን ለመያዝና አባላትን ለማፍራት ብቻ እንደ ማስታወቂያ ይጠቀሙበታል እንጂ የአሠራር መዋቅር ተከትሎ የመሄዱ ጉዳይ ገና አጠራጣሪ ነው። በሌላ መልኩ ደግሞ አንዳንድ ቅን አመለካከት ባላቸው አበው ካህናትና ምዕመናኑ በኩል እየተደረገ ያለው መዋቅር ጠብቆ የመሄዱ ትግል በጣም የሚያስደስት በመሆኑ ሊበረታታ ይገባል።

ሌላው ሁላችን የምናውቀው የቤተ ክርስቲያን መከፋፈል ጉዳይ ነው አንዱ ስደተኛ ሌላው ገለልተኛ ሌላው ቤተኛ የሚባለው የመለያየት መንፈስ ነው። እንዲህ ዓይነቱ መለያየት አደገኛነቱ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ብቻ ሳይሆን ለሀገራችን ለኢትዮጵያና ህዝቦቿ ጭምር ነው ብዬ አስባለሁ። መለያየት ጸረ ዕድገት ነው፣ መለያየት ጸረ ሥልጣኔ ነው፣ መለያየት ውድቀት ነው፣ መለያየት ድህነት ነው፣ መለያየት መጨረሻው ማንነትን አጥቶ መጥፋት ነው። /ማቴ ፲፪፥፳፭/። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን አንድ ስለሆነች ወደ አንድነት መምጣቱ ጊዜና ቀነ ቀጠሮ የሚሰጠው ስላልሆነ ይታሰብበት እላለሁ።

***ሐመረ ኖኅ፦*** ቤተ ክርስቲያናችን ሐዋርያዊ ተልእኮዋን በብቃት እንድትወጣ ለማድረግና በውጭ ሀገር አዲስ አማኞችን ለማፍራት ከቤተ ክርስቲያን አባቶችና ከምዕመናን ምን ይጠበቃል?

***ብፁዕ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ፦*** ቤተ ክርስቲያናችን ሐዋርያዊ ተልእኮዋን ለመወጣት፦

1. ከላይ ከቅዱስ ሲኖዶስ የሚወርደውን መዋቅር ጠብቆና መልካም አስተዳደርን አጠናክሮ መሥራት ይገባል።
2. ምዕመናን ሃይማኖታቸውንና ሥርዓታቸውን በታማኝነት ከአባቶች ጋር በመሆን ጠብቀው ለልጆቻቸው ማውረስ ይገባቸዋል እላለሁ።
3. ቤተ ክርስቲያን የጸሎት ቤትና ከእግዚአብሔር ጋር መገናኛ ቦታ ናት እንጂ ምድራዊና ሥጋዊ አመለካከት እንዲሁም የዘረኝነት ሀሳብ የሚንጸባርቅባት ስላልሆነች የቤተ ክርስቲያን ምዕመናንና ካህናት አውቀው ሁሉም የሚጠበቅበትን የበኩሉን ድርሻ ቢወጣ ጥሩ ነው እላለሁ።

ከላይ በዘረዘርኳቸው ነጥቦች መሠረት አገልግሎታችንን አሻሽለን ከሠራን ያሉንን የቤተ ክርስቲያናችንን አባላት በሃይማኖታቸው ከማጽናትም አልፎ ማብዛት እንዲሁም አዳዲስ አማኞችንም ለማፍራት የሚያስቸግር ነገር አይኖርም ብዬ አስባለሁ።

***ሐመረ ኖኅ፦*** ወጣቱ ትውልድ ሃይማኖቱን እንዲያውቅና ቤተ ክርስቲያንን እንዲረከብ ምን መደረግ አለበት ይላሉ?

***ብፁዕ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ፦*** ወጣቱ ትውልድ ሃይማኖቱን እንዲያውቅና ቤተ ክርስቲያንን እንዲረከብ ማድረግ ያለበት ቢኖር ወደ ቤተ ክርስቲያን መምጣት ነው። መጥቶም የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ መማር ይገባዋል። ያን ጊዜ በወጣትነት ዕድሜያቸው እግዚአብሔርን ያገለገሉትን ሊያውቅ ይችላልና፤ እነ ዳንኤልን፣ አናንያን፣ አዛርያን፣ ሚሳኤልን፣ እነ ቅዱስ ቂርቆስና ሌሎችንም በተገቢ ሰዓት ተገቢ አገልግሎት የሰጡትን አውቆና ተረድቶ በእምነትና በምግባር ሊመስላቸው ይገባል። /ዕብ ፲፫፥፯/። በአባቶች ፈንታ ልጆች ተወለዱልሽ ተብሎ የተነገረውም ለእነርሱ ስለሆነ በተባለላቸው መሠረት በትዕግሥትና በጥበብ በእምነትና በጸሎት ከተጓዙ ቤተ ክርስቲያኗን የማይረከቡበት ምንም ምክንያት የለም።

***ሐመረ ኖኅ፦*** ለምዕመናን የሚያስተላልፉት መልእክት ካለ?

***ብፁዕ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ፦*** በመጨረሻም ለምዕመናን የማስተላልፈው መልእክት ምዕመኑ ሃይማኖቱን፣ መንፈሳዊ ባህሉንና ሥርዓቱን ጠብቆ ቤተሰቦቹንም ወደ እግዚአብሔር ቤት እየወሰደ ፈሪሃ እግዚአብሔርን እያስተማረ ኢትዮጵያዊ ታሪኩንና መንፈሳዊውን ሀብት ተምሮ ሰማያዊውን በረከት ለልጆቹ በማውረስ እንደ ኖኅና ሎጥ በክፉ ዘመን ደግ፣ በኃጢአት ዘመንና በኃጢአት ከተማ እየኖረ ጻድቅ ሆኖ የአባትነት እና የእናትነት ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል እላለሁ። /ዘፍ ፮፥፰፤ ፯፥፩፤ ፲፱፥፲፪-፳፪/።

የቤተ ክርስቲያናችንን ችግር በተመለከተ ቤተ ክርስቲያን እንግዲህ ቀራንዮ ናት። ከቀራንዮ የሚገኘው ደግሞ መስቀል፣ መውደቅና መነሣት፣ ምስማርና ችንካር ናቸው። በአጠቃላይ መስቀሉን ተሸክሞ መከተል ማለት መከራውን ታግሦ በድል አድራጊነት ወደ ተራራው መንግሥተ እግዚአብሔር መግባት ማለት ነውና አንዳንድ ጊዜም ከእኛ ጠባቂዎች ከተባልነው አባቶች የሚታይ ችግር እንኳ ቢኖር ምዕመኑ ተስፋ መቁረጥ የለበትም። ለሁሉም ያለ አድልዎ እንደሥራው የሚከፍል ስላለ እስከ መጨረሻው ድረስ በሃይማኖቱ ጸንቶ፣ በምግባርና በመልካም ሥራ አጊጦ በመኖር መንግሥተ እግዚአብሔርን ለመውረስ እንዲችል መልእክቴን አስተላልፋለሁ።

***ሐመረ ኖኅ፦*** ብፁዕ አባታችን ጊዜ ሰጥተው ለጥያቄዎቻችን መልስ ስለሰጡን በእግዚአብሔር ስም እናመሰግንዎታለን። እግዚአብዚሔር ረጅም ዕድሜ፣ የተሟላ ጤንነት፣ የተሳካ የአገልግሎት ዘመን ይስጥልን።

***ብፁዕ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ፦*** አሜን፤ እግዚአብሔር የእናንተንም አገልግሎት ይባርክላችሁ፣ ለአገልግሎትም ያትጋችሁ።

***ሐመረ ኖኅ፦*** አሜን።

# ዜና

ምንጭ፡ የአሜሪካ ማዕከል የአባላትና ቀጣና ማዕከላት ክትትል ክፍል

## ዋና ማዕከል

### የስብከተ ወንጌል ማስፋፊያ ፕሮግራም ቢሮ ያከናወናቸውን ተግባራት አስታወቀ

በማኅበረ ቅዱሳን በትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ዋና ክፍል የስብከተ ወንጌል ማስፋፊያ ፕሮግራም ማስተባበሪያ ቢሮ እስካሁን ያከናወናቸውንና በቀጣይ ሊሠራ ያቀዳቸውን ተግባራት አስታወቀ። በ2001 እና 2002 ዓ.ም. ፕሮግራሙን ለምዕመናን የማስተዋወቅና የመቅረጽ ሥራ ተሠርቶ በተወሰነ ደረጃ ወደ ትግበራ ተገብቷል። በ2003 ዓ.ም. በጠቅላይ ቤተ ክህነት የትምህርትና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ ክፍል የተነደፈውን ፕሮግራም እንዲያውቅ ተደርጓል። መምሪያውም ለፕሮግራሙ ማስፈጸሚያ የሚሆን አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግ ቃል ገብቷል።

ፕሮግራሙ በዋናነት የሚያተኩረው ስብከተ ወንጌልን ለምዕመናን ማዳረስ ላይ ሲሆን የንድፈ አሳቡ መነሻ ደግሞ በተለይ በጠረፋማና ገጠራማ አካባቢ ለሚገኙ ምዕመናን ጉባዔ ማካሔድና ሰባኬ ወንጌል ከመመደብ ጀምሮ ለአካባቢው ካህናትና የሰንበት ትምህርት ቤት አመራር አባላትም የአቅም ግንባታ ሥልጠና መስጠት ነው። ፕሮግራሙ በመላው ሀገሪቱ ከሚገኙ 45 ሀገረ ስብከቶች መካከል ችግሩ ይበልጥ ይከፋል ተብሎ በታመነባቸው 20 ሀገረ ስብከቶች ሲሆን፣ በኦሮሚያና ደቡብ ክልል በሚገኙ ጠረፋማና ገጠር አካባቢዎች ልዩ ትኩረት ይደረጋል።

በ2003 ዓ.ም. ከታቀዱት ዕቅዶች መካከል በአምስት አህጉረ ስብከት የሕዝብ ጉባዔያት የተካሔዱ ሲሆን እነዚህም ጅማ፣ አርባ ምንጭ፣ ሆሣዕና ድሬዳዋና አፋር ይገኙበታል። ከእነዚህም አህጉረ ስብከት ሊቃነ ጳጳሳት ጋር ስለ አፈጻጸሙ የመግባቢያ ሠነድ ተፈርሟል። በሌላ በኩል በአማርኛና ኦሮምኛ ቋንቋዎች የተዘጋጀ ትምህርታዊ ጽሑፍ በበራሪ ወረቀት 17,000 ቅጂ ታትሞ በተለይ ለገጠር አብያተ ክርስቲያናት እንዲዳረስ ተደርጓል። እንደዚሁም በድምፅ እና ድምፅ ወምስል ካሴቶችን አዘጋጅቶ ለምዕመናን እንዲደርሱ የተደረገ ሲሆን በጅማና ኢሉባቦር አህጉረ ስብከት ደግሞ ሐዋርያዊ ጉዞ ተደርጎ 10 ቀናት የፈጁ ጉባዔያት ተካሂደዋል። በቀጣይ መጋቢት 11 ቀን 2003 ዓ.ም. በኢትዮጵያ የስብሰባ ማዕከል በተዘጋጀ ዐውደ ጥናት ፕሮግራሙ የሚካሔድባቸውን 20 አህጉረ ስብከቶች ነባራዊ ሁኔታ የሚያሳዩ እና ማኅበሩ ስብከተ ወንጌልን በማስፋፋት ረገድ የሠራቸው ሥራዎችና ዕቅዶች ቀርበዋል።

ፕሮግራሙን ተግባራዊ ለማድረግ ሕዝበ ክርስቲያን በገንዘብ፣ በቁሳቁስና በጸሎት እንዲራዱ ተጠይቋል፤ የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ የሚፈልጉ ምዕመናን አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አራት ኪሎ ቅርንጫፍ ሒሳብ ቁጥር **04024224400** ብለው መላክ እንደሚችሉ ተገልጧል።

### ከተለያዩ ሀገረ ስብከቶች የተውጣጡ ሠልጣኞች ተመረቁ

የማኅበረ ቅዱሳን ትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ክፍል ለ13ኛ ጊዜ ባዘጋጀው ሥልጠና ከተለያዩት ቦታዎች የመጡ 27 ሠልጣኞች ለሁለት ሳምንት የቆየ መሠረታዊ የሃይማኖት ትምህርት ሲከታተሉ ቆይተው የካቲት 13 ቀን 2003 ዓ.ም. ተመረቁ። ከዚህ በፊት በተካሄዱት 12 ዙር ሥልጠናዎች 219 ሠልጣኞች ሥልጠናውን መከታተላቸው ታውቋል። ሥልጠናውን ከወሰዱት በጠረፋማ ቦታዎች ከሚኖሩት ብሔረሰቦች ውስጥ ከጋምቤላ፣ ከአፋር፣ ከኦሮሚያ፣ ከቤንሻንጉል፣ ከደቡብ ኦሞ፣ ከጂንካ፣ ከሰመራ፣ ከአላባ፣ ከጠምባሮ፣ ከስልጤና ከጉራጌ ዞኖች የተውጣጡ እንደነበሩ አስታውሰው በአሁኑ መርሐ ግብር ስልጠናውን የወሰዱት ከሱማሌ፣ ከቦረና፣ ከጉጂና ሊበን ዞኖች የመጡ ናቸው።

በዚህ ሥልጠና ስለ ስነ ፍጥረት፣ ትምህርተ ሃይማኖት፣ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን፣ ነገረ ቅዱሳን፣ ክርስትያናዊ ሥነ ምግባር፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና የስብከት ዘዴ በሚሉ ርዕሶች ሥልጠናው ተሰጥቷል። በተጨማሪ ሠልጣኞቹ ታሪካዊ ቦታዎችንና ሙዚየሞችን በቆይታቸው ወቅት ጎብኝተዋል።

> **የሬድዮ ቤተሰብ አባል ለመሆን ይሻሉ?**
>
> ማኅበረ ቅዱሳን በገጠሪቱ ኢትዮጵያ እንዲሁም በከተማው ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋት በሚያደርገው ጥረት አዲስ የሬድዮ ፕሮግራም በቅርቡ ይጀምራል። ከሚከተሉት መገናኛ መንገዶች አንዱን በመጠቀም ለዓመት የ100 ዶላር፣ የ50 ዶላር፣ ወይም የ30 ዶላር አስተዋጽኦ ማድረግና የአብርሃም፣ የይስሃቅ፣ ወይም የያዕቆብ የሬድዮ ቤተሰብ አባል መሆን እንደሚችሉ በደስታ እንገልጻለን፡-
>
> eotcmkusa_hymn@yahoo.com
> (425) 442-5290
> (425) 442-3128
> (404) 932-4658

የሠልጣኞቹ ተወካዮች እንደገለጹት "በሚኖሩበት ጠረፋማ አካባቢ ያሉ ምዕመናን በመናፍቃንና በአሕዛብ የተከበቡ ሲሆን መናፍቃን በገንዘብና በሥልጣናቸው በመጠቀም የተለያዩ ሥልጠናዎችን እያዘጋጁ አብዛኛውን ምዕመን በቋንቋቸው እያስተማሩ ወደ መናፍቅነት እየለወጧቸው እንደነበርና በአንዳንድ ቦታዎች ደግሞ ምንም አይነት ቤተ ክርስቲያን ባለመኖሩ ኅብረተሰቡ በባዕድ አምልኮ ውስጥ እንደሆነ ገልጸው፤ የአካባቢው ምዕመናን መጠመቅ እንደሚፈልጉና ቤተ ክርስቲያንም ተሠርቶላቸው ቅዳሴ የሚያስቀድሱበት፣ ሥጋ ወደሙ የሚቀበሉበት፣ ጸሎት የሚያደርሱበት፣ ወንጌልን የሚማሩበት በአጠቃላይ አምልኮተ እግዚአብሔር የሚፈጽሙበት ቤተ ክርስቲያን እንዲሠራላቸው ለቤተ ክርስቲያን ልጆች ጥሪያቸውን አቅርበዋል።

### ሰባተኛው ሀገር አቀፍ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት /ግቢ ጉባዔያት/ ሴሚናር ተካሄደ

በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ በሰ/ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን 7ኛውን የግቢ ጉባዔያት ተወካዮች ሴሚናር ከየካቲት 25-27 ቀን 2003 ዓ.ም. አዲስ አበባ ላይ ተካሄደ። በሴሚናሩ 310 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት /የግቢ ጉባዔያት/ ተወካዮች የ41 ማዕከላትና ወረዳ ማዕከላት የግቢ ጉባዔያት ማደራጃና ማስተባበሪያ ክፍል ኃላፊዎች ተገኝተዋል። ሴሚናሩም ማኅበሩ በ1984 ዓ.ም. በቅዱስ ሲኖዶስ ጸድቆ በተሰጠው መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት /ግቢ ጉባዔያት/ የሚገኙ የቤተ ክርስቲያን ልጆች በማስተማርና ለቤተ ክርስቲያን ተተኪ ትውልድ እንዲሆኑ ለማብቃት እየሠራ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ሴሚናሩ

በተካሄደባቸው ሦስት ቀናት በሀገሪቱ ካሉ የከፍተኛ ተቋማት የግቢ ጉባዔያት ተወካዮች ሴሚናር ላይ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የልምድ ተሞክሮ፣ የአገልግሎት ስልትና መንፈሳዊ ሕይወት እንዲሁም በምግባረ ሰናይ ያላቸውን ተሳትፎ አጠናክረው የሚሔዱበትን አቅጣጫ መንደፍ የሚያስችል ውይይት ተደርጓል።

ማኅበሩ በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ሥር ከተቋቋመበት ከ1984 ዓ.ም. ጀምሮ ዓለም አቀፍ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በሥሩ የሚገኙ ከ120,000 በላይ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎችን የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት እያስተማረ ይገኛል።

### ማኅበረ ቅዱሳን የኅብር ሚዲያ መካነ ድር አገልግሎት ጀመረ

ማኅበረ ቅዱሳን http://multimedia.eotc-mkidusan.org በሚል አድራሻ አዲስ የኅብር ሚዲያ መካነ ድር /multimedia website/ አገልግሎት ጀምሯል። የተለቀቀው ይኸው መካነ ድር የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓት እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት የጠበቁ የምስል ወድምጽ ስብከቶችና ተከታታይ ትምህርቶች፣ ዜማዎችና፣ መዝሙራት እንዲሁም የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጓሜና ንባብ ያስተላልፋል። በተጨማሪም የቅዱሳት ሥዕላትና የቅዱሳት መካናት ፎቶዎችም ከመግለጫ ጋር ይኖሩታል። መካነ ድሩን ለአጠቃቀም ምቹ ለማድረግ የምስል ወድምጽ፣ የድምጽ፣ እና የምስል ዝግጅቶች እያንዳንዳቸው በተለያዩ ክፍሎች /ዐምዶች/ ተደራጅተው ቀርበዋል። ተጠቃሚዎች ዝጅቶቹን መካነ ድሩ ላይ በቀጥታ በማጫወት/streaming/ ወይም በማውረድ /downloading/ መጠቀም የሚችሉበት መንገድም ተመቻችቷል። መካነ ድሩ በሳምንት ከ10 ሰዓታት በላይ የምስል ወድምጽ ዝግጅቶችን ማቅረብ የሚጀምር ሲሆን የኢንተርኔት አገልግሎት በበቂ ሁኔታ ለሌለባቸው አካባቢዎች እነዚህ ዝግጅቶች በሲዲ የሚሰራጩበት መንገድም እየተመቻቸ ነው ።




## አሜሪካ ማዕከል

### ዐውደ ጥናት ተካሄደ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን በሰሜን አሜሪካ ማዕከል የዳላስ ቀጣና ማዕከል አዘጋጅነት በሂዩስተን ከተማ ለሁለት ቀናት ዐውደ ጥናት ተካሄደ። ከመጋቢት 16-17 2003 ዓ.ም. በተካሄደው በዚሁ ዐውደ ጥናት በተለያዩ ርዕሶች ላይ ውይይት የተደረገ ሲሆን ከእነዚህም፦

- የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ መዋቅራዊ ፈተናዎች አስተዳደራዊ ወይስ ሃይማኖታዊ
- የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ አድባራት፣ ገዳማትና የአብነት ትምህርት ቤቶች ከየት ወደየት
- የተሐድሶ እና የመናፍቃን ስውር እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ

የሚሉት ይገኙበታል። በዚህ ለሁለት ቀናት በተካሄደው ውይይት ላይ በሂዩስተንና አካባቢው ያሉ በርካታ ካህናትና ምዕመናን ተሳትፈዋል።

ዐውደ ጥናቱንየተሳተፉ ምዕመናን የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ መዋቅራዊ አሠራር በወቅቱ በአሜሪካ እየተሠራበት ካለው የቤተ ክርስቲያን አመሠራረትና አስተዳደር ጋር ያለውን ልዩነት እና አንድነት፣ የተሐድሶ እንቅስቃሴ በቤተ ክርስቲያን ላይ እያደረሰ ያለውን አደጋ፣ ገዳማት እና አድባራት ያሉባቸውን ችግሮች እና የሚረዱበትንም መንገድ ለመገንዘብ እንደቻሉ ገልጸዋል። በተለይም ገዳማትን እና የአብነት ትምህርት ቤቶች ያሉባቸውን ችግሮች ለመቅረፍ በማኅበረ ቅዱሳን የተጠኑትን ፕሮጀክቶች ለማገዝ ምዕመናኑ ቃል የገቡ ሲሆን ወደፊትም ተመሳሳይ ዐውደ ጥናቶች በከተማው መቀጠል እንዳለበት ለአዘጋጆቹ አስገንዝበዋል።

### ዐውደ ርዕይ በኦክላሆማ ከተማ

የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ በዋሺንግተን ዲሲና አካባቢው ሀገረ ስብከት በኦክላሆማ ከተማ የገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን እና በማኅበረ ቅዱሳን የዳላስ ቀጣና ማዕከል ትብብር ሚያዝያ 9 2003 ዓ.ም. ዐውደ ርዕይ ተካሄደ። በዐውደ ርዕዩ ላይ ካህናት፣ ዲያቆናት እና የአካባቢው ምዕመናን ተገኝተዋል። ዐውደ ርዕዩ ሰባት ክፍሎችን ያካተተ ሲሆን እነዚህም፦

- የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ታሪክ
- ቅዱሳት ሥዕላት
- ንዋየ ቅድሳት
- ዜማ
- ቅዱሳት መካናት /በዚህ ክፍል አብነት ትምህርት ቤቶችንም በተመለከተ ገለጻ ተሰጥቷል/
- ማኅበረ ቅዱሳን
- የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ነገ

የሚሉት ናቸው።

በዐውደ ርዕዩ የታደሙት ምዕመናን እጅግ በጣም እንደተደሰቱና ሰፊ ዕውቀት ያገኙበት እንደሆነ፣ ዐውደ ርዕዩ በሲዲ ተቀድቶ ቢሰራጭ ይበልጥ እንደሚጠቅም፣ ተመመሳሳይ የሆኑ ዐውደ ጥናቶች ቢዘጋጁም ጠቃሚ እንደሚሆን አስተያየታቸውን ሰጥተዋል። ከዚህም በተጨማሪ ስለ ማኅበሩ የነበራቸው ግንዛቤ እናሳ በመሆኑ ከተሐድሶ ጋር የሚያመሳስሉት እንደነበር

አስታውቀዋል። በዚህም ምክንያት ቀጣና ማዕከሉ በአካባቢው ስለተሐድሶ የሚያሳውቅ ዝግጅትችና ጉባዔያትን ማዘጋጀት እንዳለበት ተገንዝቧል። ለዐውደ ርዕዩ መሳካት የቤተ ክርስቲያኑ ካህናት፣ የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች እና አጠቃላዩ ምዕመናን ያደረጉት ትብብር ከፍተኛና ይበል የሚያሰኝ ነበር።

### የሕፃናት አስተዳደግን አስመልክቶ የምክክር ዐውደ ጥናት ተካሄደ

በምዕራብ ስቴቶችና ካሊፎርኒያ ሀገረ ስብከት አስትን፣ ቴክሳስ በሚገኘው የደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ እና በማኅበረ ቅዱሳን የዳላስ ቀጣና ማዕከል ትብብር ተተኪ ሕፃናትን እንዴት ማስተማር እና የቤተ ክርስቲያን ተረካቢ ማድረግ ይቻላል በሚል ርዕስ የምክክር ዐውደ ጥናት በደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ ግንቦት 7 ቀን 2003 ዓ.ም. ተካሄደ። ዐውደ ጥናቱ የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ዓለም አቀፋዊት እንደመሆኗ መጠን ልጆቿን ተከትላ በመላው ዓለም አገልግሎቷን እየፈጸመች መሆኗን በማስገንዘብ የዘመኑ ትውልድ አደራውን ተቀብሎ ለትውልድ ማስተላለፍ መቻሉ ታላቅ ጥያቄ ውስጥ እንደሆነ፣ ይህንንም ታላቅ ክፍተት ለመሙላት ያሉ አመቺ ሁኔታዎችን በማስረዳት በዚህ ሁኔታ ከቀጠልን "ኢትዮጵያዊነት ዘርን እንጂ ማንነትን ወደማይገልጥበት ደረጃ መሄዱ አይቀርም" የሚለው የጥናቱ ምልከታ ወላጆች በከፍተኛ ሁኔታ ተነሳስተው ልጆቻቸውን ማስተማር እንዳለባቸው እንዲወስኑ ረድቷቸዋል። በዐውደ ጥናቱ ማጠቃለያ ላይ፡-

1. ወላጆችን በቤተ ክርስቲያን ትምህርት በስለው ልጆቻቸውን ማስተማር በሚችሉበት ደረጃ ላይ እንዲደርሱ
2. ብቃት እና ፍላጎት ያላቸው የቤተ ክርስቲያን ልጆች ተመርጠው ልጆችን እንዲያስተምሩ
3. ወላጆች ገንዘብ በማሰባሰብ ለሕፃናቱ የሚያስፈልጉ መጻሕፍት፣ ሲዲ፣ ቪሲዲ እና መጫወቻዎችን እንዲያሠሩ
4. የቤተ ክርስቲያን ዕውቀት መለኪያ ውድድር /በሕፃናት መካከል/ እንዲደረግ
5. ተጠሪነቱ ለደብሩ ሰበካ ጉባዔ የሆነ የወላጆች ኮሚቴ እንዲቋቋም በመስማማት በከፍተኛ ተነሳሽነት ተፈጽሟል።

### የግንቦት ልደታ በዓል

በሲያትል፣ በዋሺንግተን ዲሲ፣ በቴነሲ እና ሌሎች ቀጣና ማዕከላት በሚገኙ አባላት የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም የልደት በዓል በደመቀ ሁኔታ ተከብሮ ውሏል። ይህ ታላቅ በዓል የእመቤታችንን ልደት በተጨማሪም የማኅበራችን 19ኛ ዓመት ታስቦ ያለፈበት ነበር። በቀጣና ማዕከላቱ በነበረው የበዓሉ አከባበር ላይ ወቅታዊ የሆኑ ጉዳዮችም ተነስተው ውይይት ተደርጎባቸዋል። ከእነዚህም መካከል፡-

- በጊዜው ስላሉ አጽራረ ቤተ ክርስቲያን
- የገዳማት እና አድባራት ሁኔታ እና እንዴት መርዳት እንደሚቻል
- የ10 ዓመቱ የስብከተ ወንጌል ፕሮጀክት
- የአባላት ሕይወትና መንፈሳዊ አገልግሎት ወዘተ... ናቸው።

### የአሜሪካ ማዕከል 13ኛው ዓመታዊ ጉባዔ

"የቤተ ክርስቲያናችንን ህልውና መጠበቅ የሁላችንም ኃላፊነት ነው" በሚል ቃል የተመራው የማኅበረ ቅዱሳን አሜሪካ ማዕከል 13ኛው ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ ከግንቦት 20-21 2003 ዓ.ም. በአትላንታ፣ ጆርጂያ ተካሄደ። በጉባዔው ላይ የዲሲ እና አካባቢው ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ አብርሃም፣ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አበው፣ ዲያቆናት ወንድሞች፣ ከ165 የማያንሱ ከተለያዩ የአሜሪካ ግዛቶች የተሰባሰቡ የማኅበሩ አባላት ወንድሞች እና እህቶች እንዲሁም ተጋባዥ እንግዶች ተገኝተው ነበር።

ጉባዔው በብፁዕ አቡነ አብርሃም በተመራ ጸሎት ኪዳን የተከፈተ ሲሆን የማዕከሉን የ2003 ዓ.ም. የሥራ ሪፖርት በማዳመጥና በሪፖርቱ ላይ ውይይት በማድረግ ተጀምሯል። በመቀጠልም "የማዕከላችን የአገልግሎት ተግዳሮቶች እና የመፍትሔ አቅጣጫዎች"፣ "የማኅበሩ አባላት ማሕበራዊ ተሳትፎ" እንዲሁም "የቤተ ክርስቲያን አንድነት" በሚሉ ርዕሶች ዙሪያ ትምህርቶች ተሰጥተው ውይይቶች ተደርገዋል። በተጨማሪም ጉባዔው በተለያዩ መምህራን በተሰጠ ትምህርተ ወንጌል እና በመዘምራን በቀረበ ጣዕመ ዝማሬ የተዋበና የደመቀ ነበር።

**ስብከተ ወንጌልን በጋራ እናስፋፋ!**

ማኅበራችን ማኅበረ ቅዱሳን ስብከተ ወንጌልን በገጠራማና ጠረፋማ ቦታዎች ለማስፋፋት የቤተ ክርስቲያንን የተለያዩ መዋቅሮች የሚያጠናክር የ10 ዓመት ፕሮጀክት ነድፏል። ይህን ታላቅ ተልእኮ ስኬታማ ለማድረግ እርስዎም በሚችሉት አስተዋጽኦ እንዲያደርጉና የበረከቱ ተካፋይ እንዲሆኑ በእግዚአብሔር ስም እንጋብዛለን። የበለጠ ለመረዳት የሰሜን አሜሪካ ትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ክፍልን ያግኙን!

**eotcmkusa_education@yahoo.com**

**(240) 899-5215**

የተዋሕዶ ድምጽ /ድምፀ ተዋሕዶ/ በሚል ስያሜ በሳምንት ሁለት ቀን የሬዲዮ ፕሮግራም ወደ ኢትዮጵያ ማስተላለፍን በተመለከተ የተደረገው ጥልቅ ጥናት ጥናቱን ባደረጉት አባላት በዝርዝር ቀርቦ ሰፊ ውይይት ከተደረገበት በኋላ በከፍተኛ ድጋፍ በቤቱ ተቀባይነትን አግኝቶ አልፏል። ይህን ስብከተ ወንጌልን በገጠሪቱ ኢትዮጵያ እንዲሁም በከተማው ለማስፋፋት የሚደረግ ጥረት ለማሳካትና ሬድዮ ጣቢያው የሚጠይቀውን ወጪ ለመሸፈን የሚያስችል ንድፈ ሀሳብም ቀርቧል፤ እሱም የአብርሃም ቤተሰብ (ለዓመት 100 ዶላር)፣ የይስሃቅ ቤተሰብ (ለዓመት 50 ዶላር) እና የያዕቆብ ቤተሰብ (ለዓመት 30 ዶላር) በሚል አባላት በመረጡት ቤተሰብ ውስጥ ተካተው ያቅማቸውን እንዲሳተፉ ዕድል የሚሰጥ፣

ላልሰሙ አባላትና ለመላው ምዕመን ደግሞ ሀሳቡን እያካፈሉ የብዙዎችን ተሳትፎ እንዲጠይቁ የሚያበረታታ ነው።

ጠቅላላ ጉባዔው በመጪው ዓመት "የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አስተዋጽኦ ለኢትዮጵያ" የሚል ዐውደ ርዕይ ይካሔድ ዘንድ የቀረበውን ዕቅድ እንዲሁም ስለ ሕጻናት ትምህርት፣ ስለስብከተ ወንጌል፣ ስለድረ ገጾች መጠናከር፣ በአሜሪካ የሚገኙትን አህጉረ ስብከት ስለመርዳት፣ ቃለ እግዚአብሔርን በመጻሕፍት፣ በጋዜጦችና በተለያዩ የሕትመት ውጤቶች ስለማሰራጨት፣ ሰንበት ት/ቤቶችን ስለመርዳት ወዘተ... በአጠቃላይ በየአገልግሎት ክፍሎቹ በ2004 ዓ.ም. ሊሠሩ የታቀዱ ሥራዎችን አድምጦና ገምግሞ አጽድቋቸዋል።

በመገንባት ላይ ያለውን የማኅበሩን ዋና ማዕከል ሕንፃ ለማጠናቀቅ የሚውል ከ56,000 ዶላር በላይ በጉባዔው ላይ ከተገኙ አባላት ተሰብስቧል።

ጉባዔውን በታላቅ ንቃት የተከታተሉት የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ አብርሃምም በሰጡት ቃለ ምዕዳን በስጋት እና በፍርሃት መሠራት ያለባቸውን ሥራዎች ከመሥራት ወደ ኋላ ማለት እንደማይገባ መክረው ማዕከሉ የጀመረውን አገልግሎት አጠናክሮ ይቀጥል ዘንድ መመሪያ ሰጥተዋል። ጉባዔው በሚከናወንባቸው ጊዜያት በሙሉ እንደማይለዩ፣ ጉዳዩ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እስከሆነ ድረስ በተልእኮው ከማኅበሩ ጎን እንደሚቆሙ በማስረዳት ጉባዔተኛውን አበረታትተዋል።

በመጨረሻም የመጪው ዓመት 14ኛ ዓመታዊ ጉባዔ በዴንቨር፣ ኮሎራዶ እንዲሆን በመወሰንና ለ15ኛውም ሚነሶታን በማጨት በጋራ ዝማሬ ጉባዔው ተጠናቅቋል።




## ባሉበት ቦታ ሆነው የተለያዩ መንፈሳዊ ትምህርቶችንና ወቅታዊ የቤተ ክርስቲያን ጉዳዮችን ማግኘት እንደሚችሉ ያውቃሉ?

ሐመር መጽሔት በየወሩ ስምዓ ጽድቅ ጋዜጣ በየ15 ቀኑ ተዘጋጅተዉ ለምዕመናን ይሰራጫሉ።
እንዲሁም በርካታ የምስል ወድምጽ ዉጤቶችና መጻሕፍቶችንም ያገኛሉ።
ለበለጠ መረጃ፦ የአሜሪካ ማዕከል የልማት ተቋማት አስተዳደር ክፍል

**eotcmkusa_development@yahoo.com**

(469) 432-1879

# ስብከተ ወንጌል

## "...እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት" /ዮሐ. ፲፭፥፲፪/

በዲያቆን አብነት አረጋ

ፍቅር የመውደድን የላቀ መጠን የምንገልጽበት ቃል ነው። መውደድ ቃል አገባቡ በመስጠትና መቀበል ሚዛናዊ አቋም ላይ የተመሠረተ ሳይሆን ያንድን ወገን ድርጊት ያሳያል። ይህ ድርጊት በሁለት ወገን መስጠትና መቀበል ሚዛናዊ አቋም ላይ ከተመሠረተ ግን መዋደድ ወይም መፋቀር ተብሎ ይገለጻል።

መዋደድን በምሳሌ ለመግለጽ የእናትና የልጅን፣ የተፋቀሩ ጥንዶችን፣ የተጋቡ ባለትዳሮችን... ፍቅር መጥቀስ ይቻላል። በዚህ የትምህርት ክፍል የምናየው ፍቅር ግን ከዚህ የተለየና ጥልቅ ነው። "...እግዚአብሔር ፍቅር ነው፥ በፍቅር የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል እግዚአብሔርም በእርሱ ይኖራል።" /፩ኛ ዮሐ. ፬፥፲፮/ እንዲል። ምክንያቱም ከላይ የጠቀስናቸውን የፍቅር ምሳሌዎች እንደ ምሳሌ ማየት ቢቻልም ምሳሌ ተመሳዩን መሆን አይችልምና በባህሪው ፍቅር የሆነ የእግዚአብሔርን ፍቅር ሊተኩት አይችሉም።

እግዚአብሔር ይህንን ባህርያዊ ፍቅሩን አዳምን ለማዳን ባደረገው ፍለጋና በከፈለው ዋጋ ገልጾታል። ይህ ፍቅር የእግዚአብሔርን ልጅ ከልዕልና ያወረደ፣ ሰው እንዲሆን ያደረገና እስከሞትም ያደረሰ ነው። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌው ለደቀ መዛሙርቱ ይህንን መውደዱን አስታውሶ የመዋደድን ትእዛዝ ሰጥቷቸዋል። "እኔ እንደወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት። ነፍሱን ስለወዳጆቹ ከማኖር ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም።" /ዮሐ. ፲፭፥፲፪/ የሚል።

ይህ ትእዛዝ ከጌታችን ለሐዋርያት ብቻ ሳይሆን ክርስትናን ለተቀበለ ወገን ሁሉ የተሰጠ ትእዛዝ ነው። ፍቅር የሆነ አምላካችን ከእርሱ ከራሱ ሰውን መውደድ በስተቀር ምንም የመወደድ ምክንያት ሳይኖረን ወዶን ፍቅሩን በመግለጽ እንድንዋደድ ያስተላለፈውን ትእዛዝ እንዴት እየፈጸምን እንገኛለን? በማለት ራሳችንን ጠይቀን ያለንን በመጠበቅ የጎደለንን ለመሙላት ከዚህ ኃይለ ቃል የእግዚአብሔርን ፍቅር፣ ከፍቅሩ የተማርንና እንድንዋደድ የታዘዝን እኛ ያለንበትን ሁኔታና ፍቅራችንን ሙሉ ለማድረግ መውሰድ የሚገባንን እርምጃ ቀጥለን እንመለከታለን። ትምህርቱን የበለጠ ግልጽ ለማድረግ ኃይለ ቃሉን ለሦስት ከፍለን እንመልከት፡-

1. እኔ ______ ወደድኳችሁ
2. እንደ
3. እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት

### 1. እኔ ______ ወደድኳችሁ

እኔ በሚል ተውላጠ ስም ራሱን የገለጸው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በዚህ ሐረግ ውስጥ ወደድኳችሁ ብሎ ከአዕምሮ በላይ በሆነ መውደዱ እንደወደደን አስታውሶ ነው የመዋደድን ትእዛዝ ከእርሱ ተምረን እንድንፈጽም የሰጠን። ለመሆኑ ከእግዚአብሔር ፍቅር የምንማረው ምንድን ነው? ፍቅሩን ልዩ የሚያደርገውስ ምንድን ነው? የእግዚአብሔር ሰውን መውደድ ከንግግር በላይ ጥልቅ፣ ከአዕምሮ በላይ ምጡቅ የሚያደርገው ምንድን ነው? እንመልከት፡-

### ሀ. ምክንያቱ

መውደድ ምክንያታዊ ነው። መውደድ ተወዳጅ ነገር ለወዳጅ ከሚሰጠው የአዕምሮ እርካታ፣ ጥቅም ወይም አገልግሎት ይመነጫል። ለምሳሌ አንድ ሰው የፅጌረዳ አበባ እወዳለሁ ቢል መውደዱ የአበባዋ መዓዛ፣ የቀለሟ ድምቀት ወይም ውበት ለአዕምሮ ከሚሰጠው እርካታ ይመነጫል።

እንግዲህ መውደድ የሚመነጨው ተወዳጅ ነገር ለወዳጅ በሚሰጠው ጥቅም፣ እርካታ ወይም ደስታ ላይ ተመሥርቶ ቢሆንም እግዚአብሔር የሰውን ልጅ የወደደው፣ ፍቅሩንም የገለጸበትን የማዳን ሥራውን የሠራው ግን ሰው እግዚአብሔርን በድሎ ጥል በነገሠበት "...ጠላቶች ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ታረቅን..." /ሮሜ. ፭፥፲/ እንዳለ ሐዋርያው ምንም የመወደድ ምክንያት ባልነበረበት ሁኔታ ውስጥ ነው። ይህ የእግዚአብሔር ፍቅር ከእርሱ ከፈጣሪ ሰውን በከንቱ መውደድ ውጭ ከሰው የመወደድ ምክንያት ያልመነጨ በመሆኑ ፍቅሩን ልዩ ያደርገዋል። "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን <u>እንዲሁ</u> ወዷልና።" /ዮሐ. ፫፥፲፮/ እንዳለ። እንዲሁም ይኸው ወንጌላዊ በመልእክቱ "ፍቅርም እንደዚህ ነው፤ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደወደደን ስለኃጢአታችንም ማስተስረያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደወደድነው አይደለም።" /፩ኛ ዮሐ. ፬፥፲/ በማለት የፍቅሩ ምክንያት አምላካዊ ቸርነትና ምሕረት እንጂ ከሰው ልጆች የሚመነጭ የመወደድ ምክንያት እንዳልሆነ አረጋግጧል።

### ለ. ፍለጋው

አዳም አትብላ የተባለውን ዕፀ በምክረ ዲያብሎስ ተታልሎ ከበላ በኋላ ከጸጋ እግዚአብሔር ተራቁቶ፣ ርስት ሀገሩን ለቅቆ ወደ መንጸፈደይን በመውረድ በእግረ አጋንንት እየተረገጠ፣ በክንዳቸው እየተቀጠቀጠ ይኖር ነበር። ይህ የባርነት ዘመን አብቅቶ የነጻነት ዘመን ይጀመር ዘንድ እግዚአብሔር በድሎና አሳዝኖት የወደቀውን የሰው ልጅ ፍለጋ ጉዞ ጀመረ። በሰብዓዊ ልምድ የበደለ ምሕረትና ይቅርታን ፍለጋ ወደተበዳይ በመሄድ በዚህም ጉዞ ለተበዳይ ክብርን በመስጠትና ጸጸቱን በመግለጽ ይቅርታን ይጠይቃል። ይህ ጉዞ ወይም ጸጸትና ይቅርታ ፍለጋ ከበደሉ ክብደት የተነሳ ይቅርታን ለማስገኘት አቅም ሲያጣም ካሳ ይጨመራል። እግዚአብሔር ግን ተበድሎ በመፈለግ የተለየ ፍቅሩን ገለጸ። ሌላው የእግዚአብሔርን ፍለጋ ልዩ የሚያደርገው ልዑል በተነሳበትና ሰው በወደቀበት መካከል ያለው የቦታ ልዩነት ነው። ይህ ፍቅር በጽርሐ አርያም የነገሠውን የእግዚአብሔር ልጅ የበደለና የጠፋው አዳምና ልጆቹን ያድን ዘንድ ከሰማየ ሰማያት ያወረደ እስከሞትም ያደረሰ በመሆኑ በእርግጥም ልዩ ነው።

### ሐ. ካሳው

በሰብዓዊ አሰራር እርቅና ሰላምን ለማምጣት የበደለ ለተበዳይ ካሳ መስጠቱ የተለመደ ነው። ይህ ካሳ ተበዳይ ያጣውን ለመተካት ብቻ ሳይሆን የጠፋውን ፍቅርም ለመመለስ ስለሚጠቅም የተገባ ነው። በእግዚአብሔር ፍቅር ውስጥ የምናየው የሰው-- የእግዚአብሔር የእርቃቸው ካሳ ግን እንደፍጥረታዊ ሥርዓት በዳይ /ሰው/ ለተበዳይ /እግዚአብሔር/ ሳይሆን ተበዳይ እርሱ እግዚአብሔር ለበደለኛው የሰው ልጅ ካሳ ማቅረቡ ፍቅሩን ልዩ ያደርገዋል። ፍቅሩን ተነፃፃሪ የሌለው ልዩ የሚያደርገው ደግሞ በራሱ ተበድሎ ከመካሱ በተጨማሪ የካሳው ዓይነት ነው። የሰው ልጅ ያጣውን ጸጋና ክብር ለመመለስ ያቀረበው መሥዋዕት፣

ቁርባን፣ ዕጣን ወዘተ… ፍርዱን ሽሮ ወደቀደመ ክብሩ ይመልሰው ዘንድ ባልቻለ ጊዜ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ዓለምን እንዲያድን ላከው። ይህ የማዳን ተልእኮ የሞተውን የሰውን ልጅ ለማዳን መሞት፣ የተዋረደውን የሰው ልጅ ክብር ለመመለስ መዋረድ፣ ከጸጋው የተራቆተውን የሰው ልጅ ጸጋውን ለመመለስ መራቆት፣ የገዢነትና የልጅነትን አክሊል ለሰው ልጅ ለማቀዳጀት የእሾህ አክሊል መቀዳጀት /ኢሳ. ፶፫፥፩-፲፤ ማቴ. ፳፯፥፳፯-፶፩/ ካሳ ሆኖ የተከፈለበት በመሆኑ ልዩ ነው።

### መ. ስለሁሉም የተከፈለ ፍቅር

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን ሥራውን የሠራው መድኃኒት የሆነ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ ልጅነትን የመለሰው ለአንድ ሰው፣ ወገን፣ ጎሳ ወይም ነገድ ሳይሆን ለሁሉም የሰው ልጅ ነው። ስለዚህም ነው ይህ ደህንነት ወደሁሉም ይደርስ ዘንድ ከትንሣኤው በኋላ ሐዋርያትን "እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም፥ እኔ እስከዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ /ማቴ. ፳፰፥፲፱-፳/ በማለት ወደ አጽናፈዓለም የላካቸው።

## 2. እንደ

"እንደ" በሁለቱ ሐረጋት መካከል የገባ የማነጻጸሪያ ቃል ሲሆን በሚያክል፣ በሚመስል ወይም በሚስተካከል የሚሉት ቃላት ሊተኩት ይችላሉ። ከላይ እንደገለጽነው እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያለው ፍቅር ልዩና ተስተካካይ የሌለው ነው። ይህ ፍቅር ተስተካካይ የለውም ስንል ሁሉን በሚችል እግዚአብሔር ብቻ የተፈጸመ ፍጡር ሊፈጽመው የማይችለው ጥልቅ ነው ማለታችን ነው። ስለዚህ ከላይ ማነጻጸሪያ ሆኖ የቀረበው "እንደ" ከዚህ የእግዚአብሔር ጥልቅ፣ አቻና ተስተካካይ የለሽ ፍቅር አንፃር ሲተረጎም የሚያክል፣ የሚስተካከል የሚሉት ቃላት ሊተኩት አይችልም ማለት ነው። ምክንያቱም ሰው ምን ቢወድ በዚህ ፍቅር ልክ ሊወድ አይችልምና ነው። ምሳሌ ከምሳሌነት አልፎ ተመሳዩን ሊሆን፣ ሊያክል ወይም ሊስተካከል እንዳይችል የኛም ፍቅር "እግዚአብሔር ፍቅር ነው" /፩ኛ ዮሐ. ፬፥፲፮/ እንዳለ ወንጌላዊው በባህሪው ፍቅር የሆነ የእርሱን መውደድ ሊያክል ወይም ሊስተካከል ባይችልም ምሳሌ አድርገን የምንፈጽመው ሊሆን ይገባል።

## 3. እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት

ይህች ትእዛዝ ሊቀ ነቢያት ሙሴ በደብረ ሲና ከተቀበላቸው ትእዛዛት አንዷ ናት። "ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ" /ዘሌ. ፲፱፥፲፰/ የምትል። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌ በነበረበት ዘመን ከሕግ የትኛዋ ትበልጣለች ተብሎ ለቀረበለት ጥያቄ ሲመልስ "ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህ በፍጹም አሳብህም ውደድ። ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች፥ እርሷም፡- ባልንጀራህን እንደነፍስህ ውደድ የምትለው ናት። ኦሪትና ነቢያት በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ጸኑ።" /ማቴ. ፳፪፥፴፯-፵/ በማለት መልሶ ነበር። ከዚህ የምንረዳው የምንፈጽማቸው ትእዛዛትና የምናደርጋቸው ምግባራት የቆሙበት መሠረት ፍቅር መሆኑን ነው። /፩ኛ ቆሮ. ፲፫፥፩-ፍጻሜው/። ይህ ፍቅር እግዚአብሔርንና ባልንጀራ የተባለ የሰውን ልጅ ሁሉ በመውደድ በዚህም መውደድ ትዕዛዛትን በመፈጸም ይገለጻል። ስለዚህ ይህች ትእዛዝ በራሷ ትእዛዝ ብቻ ሳትሆን የትእዛዛት መሠረት ናትና ትእዛዛትን በግዴታ ሳይሆን በዚህ የፍቅር መሠረት ላይ ቆመን ለመፈጸም ይገባናል። "በክርስቶስ ኢየሱስ ሆኖ፥ በፍቅር የሚሠራ እምነት እንጂ መገረዝ ቢሆን ወይም አለመገረዝ አይጠቅምምና" /ገላ. ፭፥፮/ እንዳለ ሐዋርያው። እንግዲህ ክርስቶስ በቃልና በድርጊት ባስተማረን ፍቅር እንዴት እንኑር? ዘርዝረን እንመልከት።

### ሀ. ምክንያት

ፍጥረታዊ ፍቅር የሚመሠረተው በመስጠትና መቀበል መርህ ላይ ነው። የምንቀበለው ወይም የምንሰጠው ነገር በራሱ ፍቅር ከመሆን አልፎ ቁስ ሊሆን ይችላል። ፍቅር ደግሞ በገንዘብ /በጥቅም/ ሊገዛ የማይችል መንፈሳዊ ኃይል እንጂ ሸቀጥ አይደለምና ገንዘብ /ጥቅም/ ፍቅርን ሲቀላቀሉት ፍቅር ስሙ ብቻ ይቀርና ጥቅም ፍለጋ እየነገሠ ይሄዳል። "ጸጉራም ውሻ አለ ሲሉት በረሃብ ይሞታል" እንዲሉ አበው ይህ ስም የቀረው ፍቅር ያለ ቢመስልም ጥቅሙ ያለቀ ወይም ፍትሐዊ አይደለም ተብሎ የታሰበ ዕለት በፊቱኑ ጥቅም እንጂ ፍቅር አይደለምና የጦርነት ሜዳ ይሆናል። ይህ ዓይነቱ ማስመሰል ዛሬ ከተራ ቅርርብ፣ ጉርብትና፣ ጓደኝነት አልፎ ትዳር በሚባለው መንፈሳዊ ተቋም ውስጥም ይስተዋላል። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተከለለን መሠረት ግን ይህ አይደለም። አምላክ ወልደ አምላክ እርሱ አዳምና ልጆቹን ምንም የመወደድ ምክንያት ሳይኖረን እንደወደደን ሁሉ እኛም እርስ በርሳችን ዝምድናን፣ ጥቅምን፣ ዘርን፣ አካባቢን ወይም የትምህርት ደረጃንና የገቢ አቅምን ወዘተ… መስፈርት ሳናደርግ የሰውን ልጅ ሁሉ ልንወድ ይገባናል። ክርስቶስ እስከሞት የወደደውን የሰው ዘር ሁሉ ክርስትናን የተቀበለ ክርስቲያን ሊወድ ይገባዋልና።

### ለ. ሁሉን መውደድ

ክርስቲያናዊ ፍቅርን ከፍጥረታዊ ፍቅር የሚለየው አንዱ ምክንያት ፍትሐዊነቱ ነው። የሰው ልጅን የወደደ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሞተው ለመላው የሰው ልጅ ይልቁንም ከስሰውና ሰቅለው ለገደሉትም ጭምር ነው። ዛሬም ለሚያምኑም ለማያምኑም ፀሐይና ዝናብን እኩል እየሰጠ ዘር መከርን ባርኮ ዓለምን በፍትሕ ይገዛል። እርሱ የፍቅር አምላክ ለእኛም "እኔ ግን እላችኋለሁ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ የሚረግሟችሁንም መርቁ፥ ለሚጠሏችሁም መልካም አድርጉ፥ ስለሚያሳድዷችሁም ጸልዩ፤ እርሱ በክፉዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና። የሚወዷችሁን ብትወዱ ምን ዋጋ አላችሁ? ቀራጮችስ ያንኑ ያደርጉ የለምን? ወንድሞቻችሁንም ብቻ እጅ ብትነሡ ምን ብልጫ ታደርጋላችሁ? አሕዛብስ ያንኑ ያደርጉ የለምን? እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ።" /ማቴ. ፭፥፵፬-ፍጻሜው/ ብሏል።

እንግዲህ ክርስቲያኖች የተቀበልናት የፍቅር ትእዛዝ ወዳጅ እንጂ ጠላት የሌላት ሁሉን በመውደድ የምትገለጥ ፍትሐዊት ናት ማለት ነው። ስለዚህ ክርስቲያኖች የማንወደው ሊኖር አይገባም። እንኳን ለጥላቻ ምክንያት የሌለንን ሰው ቀርቶ እየጠላ የሚያሳድደንን እንኳ እንድንወድ ታዝዘናልና።

በዚህ ቃል ላይ በተመሠረተች ቤተ ክርስቲያን ወይም በእኛ ሕይወት ውስጥ ዛሬ ይህ ፍሬ ይስተዋላል ወይ? በደሙ የተመሠረተች ቤተ ክርስቲያን ወደዚህ ሕይወት ለሚመጡ ሁሉ ክፍት ናት። የመጡትን ትሰበስባለች፣ ያልመጡትን ትፈልጋለች፣ እንዲመጡም ትጸልያለች። ዛሬ ፍቅራችን የተመሠረተበት "ሁሉንም ውደዱ" አምላካዊ ትእዛዝ ተሸርሽሮ እንኳን የሚገድሉ

የሚያሳድዱንን አሕዛብ ልንወድ ክርስቲያኖች እርስ በርሳችን ልንዋደድ አልቻልንም። እንኳን እስከ አጽናፈዓለም ሄደን ያላመኑ ልናሳምን ያመኑ ለመግባት ዘር ወይም የአካባቢ ተወላጅነት የሚጠየቁባቸው አብያተ ክርስቲያናትን እየተከልን፤ በውስጣቸው ታቦተ ሕግ እያለ በቅዱሳኑ ስም ሳይሆን በግለሰቦች ስም የሚጠሩ አብያተ ክርስቲያናትም እንደሱቅ ከተሠራልን ሥርዓት ውጪ እይከፈትን ቤተ ክርስቲያንን እያፈረስን ገነባናት የምንልበት የጥላቻ ዘመን ላይ ደርሰናል። በእርግጥ እግዚአብሔር በዚህ የጥላቻ አገልግሎት ይደሰት ይሆን? ወይስ እንደእስራኤላውያን እግዚአብሔርን እያገለገልነው ነው እያልን ከጸጋው እየራቅን በከንቱ እይደከምን? /ሮሜ. ፲፥፫/

ዛሬ ቤተ ክርስቲያንን የገጠማት ይህ ጥቁር ታሪክ የተፈጸመው በእኛ ደካማነት ነው። ይህን ጥቁር ታሪክ በወርቃማ የፍቅርና የሰላም ቀለም ደምስሶ፣ የተከልነውን አረም በመንቀል፣ ጥልን ገድሎ ከአባቶቻችን የተቀበልናትን ንጹሕ ሃይማኖት ለትውልድ ለማስተላለፍ ዛሬ ወደሕሊና መመለስና ፍቅርና ሰላምን የሚያመጣ ክርስቲያናዊ ዋጋ መክፈል ያስፈልጋል።

## ሐ. ይቅርታ

ክርስቲያን ቢቻለው ከሁሉም ጋር በሰላም ሊኖር ይገባዋል። ይህ ባይሆን የሰላም እጦትና የአለመግባባቱ ምክንያት እርሱ ሊሆን አይገባውም። ይልቁንም እየተጠላ ይወዳል፣ እየተረገመ ይመርቃል፣ እየተሳደደ ይጸልያል ወዘተ... በመጥላት ውስጥ የሚወድ፣ እየተረገመ የሚመርቅ፣ እየተሳደደ የሚጸልይ ወገን ደግሞ ፍቅሩ ፈተና የማያሸንፈው ፍጹም ነውና በደለኛ ሆኖ የጸቡ ወይም የአለመግባባቱ ምክንያት ሊሆን አይችልም። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚጠሉንን እንድንወዳቸው ብቻ ሳይሆን ይቅርታ የሚጠይቅ ልብ አግኝተው ይቅርታ ቢጠይቁን ይቅር እንድንላቸው "እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን" /ማቴ. ፮፥፲፪/ ብለን እንድንጸልይ አስተምሮናል። አንድም ከዚህ የጸሎት ቃል የምንማረው ክርስቲያን ተበድሎ ይቅርታ የሚጠየቅና ይቅር የሚል እንጂ በድሎ የጸቡ ምክንያት በመሆን ይቅርታ የሚጠይቅ ወይም ተበድሎ ይቅርታ ቢጠየቅ አሻፈረኝ የሚል ሊሆን እንደማይገባው ነው።

በሌላ በኩል መድኃኒታችን ለሰው ልጅ ይቅርታ ያደረገው በአዳምና በልጆቹ በደል ምክንያት የሰው ልጅ የይቅርታ ጥሪ ወደእግዚአብሔር ጸባዖት እንዳይደርስ ኃጢአት ግድግዳ በሆነችበት ሁኔታ ነበር። /ኢሳ. ፶፱፥፩-፰/። ስለዚህ እርቁ የተፈጸመው በሰው ልጆች የይቅርታ ጥያቄ ሳይሆን በእግዚአብሔር ቸርነት ነው ማለት ነው። እኛም እንኳን በድለን ቀርቶ ተበድለንም ይቅርታ ጠይቀን ፍቅሩን ብንመልሰው ከፍቅሩ የተማርን እንሆናለን። ዛሬ ክርስቲያናዊ ሕይወታችንን የጎደለው ትልቅ መንፈሳዊ እሴት ይቅርታ ነው። በድለን ይቅርታ የማንጠይቅ፣ ተበድለን ለሚቀርብልን ይቅርታ ደጅ የምንዘጋ /፪ኛ ጢሞ. ፫፥፩-፬፤ ሮሜ. ፩፥፳፱-፴፪/ በቂምና በጥላቻ ውስጥ እግዚአብሔርን ለማስደሰት በከንቱ የምንደክም፣ በድርጊት የማንኖርበትን ሰላም የምንሰብክ ብዙዎች ነን። ስለዚህ ወደልቦናችን ተመልሰን የበደለንን ይቅርታ በመጠየቅ የተበደልንም ለፍቅርና ለሰላም ስንል ይቅርታን በመስጠት ያጣነውን ሰላም ልንመልስ ይገባናል።

## መ. ካሳ

ሰው ቢበድል መካስ ይገባዋል። ካሳ ማለት ለጥፋት የሚከፈል ዋጋ ማለት ነው። የካሳ የመጀመሪያው ክፍል ጸጸት ነው። ሰው አጠፋሁ ብሎ ሳይጸጸት ልታረቅ ልካስ ቢል ማስመሰል እንጂ መታረቅ አይደለምና ጸጸት የካሳው የመጀመሪያ ክፍል ይሆናል። ጸጸትን የሚከተለው የካሳ ክፍል ደግሞ ውሳኔ ነው። ተሳስቶ በስህተቱ የተጸጸተ ሰው ዳግም ላለመበደል ወስኖ ለውሳኔው በመኖር በፍቅሩ የሚክስ ሊሆን ይገባዋል። ከዚህ በኋላ ነው ቁሳዊ ካሳ የሚጠበቀው። ከጌታችን የምንማረው ግን ከዚህ ይልቃል። ያልበደለ እርሱ ሊካስ ሲገባው ለበደለኛው የሰው ልጅ ገንዘብ ወይም ቁሳዊ ሀብት ሳይሆን ክቡር ሕይወቱን ካሳ፣ ሥጋውንና ደሙን የሕይወት ምግብና መጠጥ አድርጎ በመስጠት እንድንድን አድርጎናል። በዚህም ከእርሱ ፍቅር ተበድሎ መካስን ተምረናል። ስለዚህ ተበድለን በመካስም ጭምር እርሱ እንደወደደን ልንዋደድ ይገባናል።

ለእኛ ለክርስቲያኖች ፍቅር የሚለው ቃል ተርታ ቃል አይደለም፤ ፍቅር እግዚአብሔር ነውና። በዚህ ቃል ውስጥ በድለን ብንጠፋ ክብሩን ጥሎ የፈለገንን እኛን ለማዳን ሰው የሆነውን እግዚአብሔርን እናየዋለን። የቤተልሔም ልደቱን፣ የግብጽ ስደቱን፣ የገዳመ ቆሮንቶስ ጾሙን፣ የጌቴሴማኒ እንግልቱን፣ አጥንቱ እስኪታይ ድረስ የተገረፈውን ግርፋት፣ የእኛን ገበና ይሸፍን ዘንድ ተራቁቶ በመስቀል ላይ መዋሉን እናስባለን። ነፍሱን ስለእኛ ሰጥቶ ሥጋውን ምግባችን ደሙን መጠጣችን አድርጎ መስጠቱን በአጠቃላይ ነጻነታችንንና ለዚህ ነጻነት የተከፈለውን ክቡር ዋጋ እንመለከታለን። በዚህ ሁኔታ የወደደን አምላክ ደግሞ የመዋደድን ትእዛዝ ሰጥቶናል። ስለዚህ እርሱ በከንቱ እንደወደደን በከንቱ በመዋደድ፣ ተበድለን ይቅር በማለት ብቻ ሳይሆን በድለንም ይቅርታ በመጠየቅና በመካስ ፍቅሩን በምትመስል ፍቅር ልንዋደድ ይገባናል።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር


**መተርጉማን ይፈለጋሉ!**

በማኅበረ ቅዱሳን አሜሪካ የትምህትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ክፍል የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት የሚገልጡ ትምህርቶችን፣ መጻሕፍትን፣ በራሪ ጽሑፎችን ወደተለያዩ ሀገር ቋንቋዎች ተርጉሞ ለምዕመናን ማቅረብ ይፈልጋል።
በዚህ የተቀደሰ አገልግሎት ላይ መሳተፍና ማገዝ ለምትፈልጉ ሁሉ ለትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ክፍሉ ኢ-ሜይል ብታደርጉልን በደስታ እንቀበላለን።

እግዚአብሔር ይስጥልን
በአሜሪካ ማዕከል የትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ክፍል
**eotcmkusa_education@yahoo.com**

## ኪነ ጥበባት

በመቅደስ አያሌው /ከሳውዝ አፍሪካ/

### ኃይሌን መልስልኝ

ጧት በማለዳ
ቤትህ ስገሰግስ
ሳልታክት ዘወትር
አንተን ሳገለግል
ስምህን ሳወድስ
ያኔ ኃይል ነበረኝ
ጸጋህም በዝቶልኝ
ስንፍና ርቆልኝ
መሰልቸት የለብኝ
አሁን ግን ጌታ ሆይ
ደሊላ ደልላኝ
ጉልበቴ ብርክ ይዞት
ኃይሌን አሳጥታኝ
እንደው ላታዛልቅ
በጥላቻ አፍቅራኝ
በጭንቀቴ ላትደርስ
ለጠላቴ ሰጥታኝ
በምርኮ አለሁና
በኃጢአት ተከብቤ
አንተን እንዳመልክህ
ተመልሶ ልቤ
እንደው ለአንድ አፍታ
ኃይሌን መልስልኝ
የኃጢአቴን ምሰሶ
ነቃቅዬ ጥዬ
የአንተ ሆኜ ልገኝ።

### የተሳትፎ ጥሪ

የሐመረ ኖኅ ኤሌክትሮኒክስ መጽሔት ዝግጅት ክፍል በኪነ ጥበባት ዓምድ ለሚቀርቡ ጽሑፎች አንባቢያንን ለማሳተፍ አቅዷል። ስለዚህ ዝንባሌና ችሎታው ያላችሁ አባላት ብትልኩልን በደስታ እንደምንቀበል እንገልጻለን። የኢ-ሜይል አድራሻችን፡- **mk.edulit@gmail.com**

### ተሸከሜ አልጋዬን

ጠዋት በማለዳ
ቤትህ እንዳልገሰግስ
ሌሊት እንደ ዳዊት
ስምህን እንዳልቀድስ
ካልጋዬ ጋር አስሮ
የያዘኝን ደዌ
የድብርት ብርድ ልብስ
የእንቅልፍ አባዜ
አርቅልኝና
ተሸከሜ አልጋዬን
ዘወትር በቤትህ
ላሰማ ጩኸቴን።




### የልቤ ማድጋ

ዘወትር ጠዋት ማታ
ስለፋ ስተጋ
እሞላለሁ ብዬ
የልቤን ማድጋ
ዛሬ በንስሐ
ሞላችልኝ ብዬ
በሐሰት ስቦርቅ
አይሎ ደስታዬ
ነገ ዳግም ባዶ
ወና ሆና ሳያት
ኀዘኔ በርትቶ
ስሞክር ልሞላት
ጠብም ላይልላት
ዳግም እየሞላች
ዳግም ስትጎድል
ምሬቴ አይሎ
ደክሜ እንዳልዝል
ከዚያ ከምንጩ ዳር
አግኝቼህ አምላኬን
ዳግም ላይጎድልብኝ
ሞልተህ ማድጋዬን
ለስምህ ልዘምር
ላብዛ ምስጋናዬን።

## ለሕፃናት

### Love One Another

By Dn. Alemayehu Desta

Our Lord Jesus Christ had twelve disciples who used to follow Him everywhere and learn from Him. They used to ask Him many questions, and He would answer them all for them. He taught them about faith, prayer, fasting, God's commandments, love and all that they needed to know so that they could also go and pass on His teaching to others.


Once upon a time, He washed the disciples' feet, and said to them, "I have given you an example so that you should do as I have done to you." (John 13:15). He taught them by example to humble themselves and serve each other. He said, "This is my commandment to you, love one another as I have loved you." (John 15:12).

This example and commandment is also for us—to love our parents, our brothers and sisters, our friends, our neighbors and all children of God. How do we fulfill this commandment?

- Through obedience to our parents, teachers and elders we show our love. A servant of God, Saint Paul said, *"Obey your parents in all things, for this is well pleasing to the Lord."* (Colossians 3:20).
- We show our love to our friends, brothers and sisters by sharing with them what we have.

As our Lord Jesus gave us an example, we should also give examples to others through different acts of love. Can you think of any other ways you can show your love to others? Our Lord Jesus Christ told the disciples different parables (stories) with examples of love. Ask your parents to read for you one of these parables, called ***"The Good Samaritan"*** from the ***Gospel of Luke***, Chapter 10:25–37, and complete the following puzzle based on the parable:

1. A certain ______ asked Jesus about what he should do to inherit eternal life.
2. We have a commandment to love the Lord ______ with all our heart.
3. We also have a commandment to love our _______ as ourselves.
4. The man whom some thieves wounded was travelling from ______ to Jericho.
5. A certain _______ had compassion on the person who was wounded by thieves.
6. The Samaritan poured _____ and wine and bandaged the wounds.



**በአስተያየትዎ ለመጽሔቷ ጥራት የድርሻዎን ይወጡ**

የሐመረ ኖኅ የኤሌክትሮኒክስ መጽሔት በአሜሪካ ለሚኖሩ ምዕመናን የመረጃ ምንጭ፣ የትምህርተ ወንጌል ማዕድ፣ የልምድ መለዋወጫ ስልትና የማዕከሉ መልእክት ማስተላለፊያ መሣሪያ መሆንን ዓላማዋ ያደረገች መጽሔት ናት። መጽሔቷን ከዚህ አንፃር እንዴት ይመዝኗታል? ምን ብናደረግ ይበልጥ ጥሩ ልናደርጋት እንችላለን? አስተያየትዎ ለመጽሔቷ ጥራት እጅግ ይጠቅማልና ይላኩልን። የኢ-ሜይል አድራሻችን፡- **mk.edulit@gmail.com**

### Solution to the Crossword Puzzle

